# ጋሼ ፒፓና የቱቢንገኑ  የድጋፍ ሰልፍ

ከበልጅግ አሊ

አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ ሰፈራችን አንድ በጣም ዘናጭ ሰው ነበር።ጊዜው ቢረዝምም እንኳ የሰውየው ለየት ያለ ባሕሪይ ከማልረሳቸው ትውስታዎች ውስጥ እንድመድበው አድርጎኛል።በወቅቱ ሬኖ መኪና አድናቆትን ያተረፈችበት ጊዜ ነበርና ይህ ግለሰብ ሬኖ ገዝቶ በትንሺ ሰፈራችን ውስጥ እንደልቡ ይሆን ነበር። ታዲያ የመኪናዋን አዲስነት ለማድነቅ በጉጉት የሚጠጉትን  ሕፃናት በእግሊዘኛ ኢዲየትስ (Idiots)፣ ዞር በሉ፣ እንዳታበላሹ እያለ ይሳደብ ነበር። ሰውየው  በዛች ሬኖ መኪናው ከኋላው የኮፍያ ማስቀመጫ አጠገብ የእንግሊዘኛ መፅሄት ( News Week , Time ) ማስቀመጥ ያዘወትራል። በሰፈራችን ውስጥ መኪናም ስላለውና የእንግሊዘኛ ዕውቀትም አለው ተብሎ ስለሚገመት አንቱ ተብሎ ይከበር ነበር። ይህ ግለሰብ የእንግሊዘኛ መፅሔት ከመኪናው የኋላ መቀመጫ ፣ በእግሩ ሲጓዝ ደግሞ የእንግሊዘኛ ጋዜጣ ( Ethiopian Herald  ) በእጁ ይዞ  የተመለከተው ሁሉ  “ይህ ሰው ታላቅ ምሁር“ ነው ብሎ ይደመድማል። ግለሰቡ ፒፓ የሚባል ሲጋራ ማጨሻ ከእጁ ስለማይለይ “ጋሼ ፒፓ“ ብለው የሰፈሩ ሰዎች ቅፅል ስም ሰጥተውት ነበር።ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የደርግ ዘመን ይመጣና የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ይጀመራል። ያልተማረ ይማር ተብሎ አዋጅ በመውጣቱ ያልተማሩ ሁሉ እንዲማሩ ተደረገ።እናቶቻችን የእድሜያቸው መግፋት፣በጤና መታወክ፣ በቤት ውስጥ ሥራ መብዛት፣ በሌሎችም ምክንያቶች በማሳበብ መሠረተ ትምህርት መማር ግዜ ማጥፋት ነው ብለው ስለሚያምኑ ላለመሄድ ጥረት ያደርጉ ነበር። እነዚህ እናቶች በቀበሌ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ይገደዳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ማይም ላለመባል የሚፈልጉ ሰዎችም ሲሸሽጉ በቅርብ በሚያውቁዋቸው እየተጋለጡ ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ይገደዳሉ።

የመደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን በትርፍ ጊዜያቸው መሰረተ ትምህርት ሰለሚያስተምሩ ወጣቶች ቢረዱዋቸውም እንኳ ዋናውን የኮሚቴ ሥራ የሚያከናውኑት እነርሱ ነበሩ።ትምህርቱ በቀጠለበት አንድ ምሽት  አንድ  መምህር የነበረ የቅርብ ጓደኛዬ ትንፋሹ እየተቋረጠ ፣ መተንፈስ አቅቶት ወደ ቤቴ እየሮጠ ይመጣል። ገና ሳይቀመጥ በቁሙ “ጉድ ነው ፣ጉድ ነው“ እያለ አፉን ይዞ ይስቃል። በመገረም ሲቃ ምንም ሊነግረኝ አልቻለም። እንደው እንደ አበደ ሰው አንዴ ይነሳል አንዴ ይቀመጣል። በወቅቱ የታመመ መስሎኝ ደነገጥኩ።  አይ ጓዴ ምን አገኘው አሞት ይሆን ብዬ ጨንቆኝ ትኩር ብዬ እመለከተው ጀመር።

“ምን ሆንክ አትናገርም እንዴ“ ? ብዬ ጠየቅሁት።
“ጉድ ነው ! ጉድ ነው ! ባትሰማው ይሻልሃል“ ብሎ ተቀመጠ።
ሻይ አፈላሁለትና እንዲጠጣ እየጋበዝኩት “ንገረኝ ምንድነው ጉዱ“ „አልኩት።
እንዴ ሻዩን ቀመሰና ዞር ብሎ  ማንም እንደሌለ ካረጋገጠ በኋላ “ጋሼ ፒፓ ማይም ነው“ አለኝ።
“አትቀልድ ምን ማለትህ ነው? ይህንን ስም ማጥፋትህን አቁም ። የሰማ እንደሆነ በሕግ ያስጠይቅሃል“ አልኩት።“አብዮት ጥበቃ ጠርቶ ያስቀፈድድሃል። ፍርድ ሸንጎ እንደሆን እድሜ ልክ ነው የሚፈርድብህ“ ብዬ ማስፈራራቴን ቀጠልኩ።
“እውነት ነው ባክህ ተወኝ“ ብሎ አፉን ይዞ በመገረም ኩርምት ብሎ ተቀመጠ።
“ከየት አገኘሽው ይህንን ወሬ“ ?
“ዛሬ ጋሼ ፒፓ ያባረራት ሠራተኛው ደሞዝዋን አልከፍልም ሲላት እኛ ጋ መጥታ ማይም መሆኑን ጠቆመች።ብናስፈራራትም ፣ውሸት ከሆን እድሜ ልክ ከርቸሌ ትማቅቂያለሽ ብንላትም ቃልዋን ልትለውጥ አልቻለችም። እንዲውም ምስክር ከፈለጋችሁ ብላ ሌላ ጓደኛዋን ጠራች። ጓደኛዋንም ብንጠይቃት እውነት ነው ብላ መሰከረች“።
“ታዲያ እናንተ ምን ልታደርጉ ነው“? አልኩና ጠየቅሁት።
“ብዙ ክርክር ተነስቶ ነበር ። የቀበሌው ሊቀመንበር ጋሼ ፒፓ ለአዲሱ ቀበሌ ማሰሪያ ብዙ ገንዘብ ያዋጡ ናቸውና ይህንን ስም ማጥፋት መቀበል የለብንም ብሎ ነበር። በድምፅ ብልጫ ተሸነፈና እኔ የለሁበትም እናንተ እንደፈለጋችሁ አድርጉት ብሎ ሄደ። ኮሚቴውም ነገ ጋሴ ፒፓ ተጠርቶ መጥቶ በኮሚቴው ፊት እንዲፈተን ወሰነ“።

ለጋሼ ፒፓ ሁላችንም ስንጨነቅ አደርን ።መንጋት አይቀርምና ነጋ። ጋሼ ፒፓም ተፈትኖ መጻፍም ማንበብም እንደማያውቅ ተረጋገጠ።መሠረተ ትምህርት እንዲማር ተገደደ። ግን በትምክህት የተሞላው ልቡ የእንግሊዘኛ መጽሄት በያዘ እጁ የጃለታ ጃፋሮን የመሠረተ ትምህርት መፅሐፍ ለማያዝ

አልፈቀደለትም።በዚያች አዲስ ክስተት በየቀኑ በሚደርስባት ሠፈር የጋሽ ፒፓ ወሬ ለሳምንታት ዜና ሆኖ ከረመ። በተከበረበት ሠፈር መዋረድን ስላልፈለገ ሠፈሩን ለቀቀ።ከዛ በኋላ ምን እንደሆነ ግን እኔም ሆንኩ መምህሩ ጓደኛዬ አልሰማንም።

ዛሬ ታዲያ ይህ ጨዋታ ትዝ ሊለኝ የቻለው አይጋ ፎረም (Aiga Forum ) በሚባለው የወያኔ ድኅረ ገፅ ላይ ያለውን ፎቶ ስመለከት ነው። በዚህ ድህረ ገፅ ላይ ሰሞኑን ጀርመን ሀገር ውስጥ ቱቢንገን ከተማ ላይ በአውሮፓ የሚገኙ የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት(TPLF) አባላት የወያኔ መንግሥትን በመደገፍ ሰልፍ እንደወጡ አትቶ የሰልፈኞቹን ተሳትፎ የሚያሳይ አባሪ ፎቶግራፍ አውጥቷል። ልብ ብዬ ስመለከት አንድ የማውቀው ሰው ፊት በስክሪኑ ላይ ብቅ አለ።ለበዓል ወይም ለሠርግ የታደመ ይመስል በደንብ ለብሶ ከሰልፉ ፊት ለፊት አስተናጋጅ ሆኖ ቆሟል።

ይህ ፎቶውን ያየሁት ግለሰብ ማንበብና መፃፍ እንደሚቸግረውና በእጁ የያዘውን መፈክር እንደማያነበው አሣምሬ አውቃለሁ። ግለሰቡ ወደ አውሮፓ የመጣው ወያኔና ሻዕብያ አባላቶቻቸውን ወደ አውሮፓ እየላኩ ሠርተው በገንዘብ እንዲደግፉዋቸው በአወጡት ፕሮግራም ነው። የግለሰቡን የደለበ ማይምነት የሠላሳ ዓመት የአውሮፓ ኑሮ ሊጥሰው አልቻለም። ሰልፉ ስለምን እነደሆነ ለማወቅ ግለሰቡ የትምህርት ደረጃው እንደማይፈቅድለት ግልጽ ነው። ሰልፉ ላይ እንዲሳተፍ ያደረገው የብሄረሰብ ጉዳይ ብቻ ሆኖ ነው የሚገኘው። ይህ ግለሰብ አለባበሱን አሳምሮ ሳየው ጋሼ ፒፓ ትዝ አለኝ።ዝነጣ የማይምነት መደበቂያ ሊሆን እንደሚችል ከዚህ በፊት በጋሼ ፒፓም ተምሬአለሁ።ጋሼ ፒፓ የእንግሊዘኛ መፅሄትና ጋዜጣ ጀርባ ማይምነቱን ደብቆ የተማረ በመምሰሉ የሠፈሩን ሰው አታለለ።ሰልፈኛው ግለሰብ ደግሞ በእጁ በያዘው መፈክር ማይምነቱን ሊደብቅ እየጣረ ነው። በአውሮፓ የሚገኙት የወያኔና የሻዕብያ ደጋፊዎች ከሱዳን ወደ አውሮፓ ከመጡ በኃላ እንኳ ለመማር ጥረት አላደረጉም። በኋላቸው የመጡ ብዙ ግለሰቦች ለትምህርት ትኩረት በመስጠታቸው የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

እንደዚህ ያሉ ግለሰቦች ሻዕቢያና፣ወያኔ የዘረኝነት ዓላማቸው ማስፈፃሚያ አድርገው የሚጠቀሙባቸው ከትምህርት ርቀው ነገሮች በሚዛናዊነት ከማየት ይልቅ በጭፍን እንዲደግፏቸው ሲያደርጉ ብቻ ነው።ትምህርትም ብቻ ሳይሆን እኒህ ግለሰቦች ተፈጥሮ የሰጠቻቸውን የማመዛዘን ፀጋ ተጠቅመው ክፉውን ከበጎ ፣ ጠቃሚውን ከጎጂ፣ ለይተው እንዳይራመዱ በመርዘኛው የዘረኝነት ቅስቀሳቸው ምንነታቸውን እንዲዘነጉ (Brain wash) ስለሚደረጉ የወያኔን ክፉ ዓላማ በፈታአውራሪነት እያስፈፀሙ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ በማንኛውም ግለሰብ ላይ መፈፀም የሌለበት ኢ- ሰብአዊ ድርጊት ነው።እንደ ወንጀልም ሊቆጠር ይገባል።ወያኔና ሻዕብያ ከእነዚህ ታማኝ አባሎቻቸው ለብዙ ዓመታት አተትርፈዋል።የገንዘብ ምንጫቸው እነዚህ ግለሰቦች እንደነበሩ የሚታወቅ ነው።

በወያኔ ተቃዋሚዎች በኩል ደግሞ ማስተማር የሚገባቸው ምሁሮች በየደኅረ ገፁ በእንግሊዘኛ ሲፈላሰፉ ስመለከት ይህ ሁሉ ለማን ነው የሚል ሃሳብ ይመጣብኛል። እርስ በእርሳቸው በአለሁ ባይነት መፏደዳቸውን ነው አጉልቶ የሚያሳየን። በየድኅረ ገፁ በእንግሊዘኛ የሚፅፉት ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች በዓላማ ፅናት የተወቀውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ ላመግኘት ቢጥሩ ፣ወያኔና ሻዕብያ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውነት ላይ እያደረሱ ያሉትን ጉዳትንና መፍትሄውን ሕዝቡ በሚረዳበት ቋንቋ ቢያስረዱ የበለጠ ጠቃሚነት ይኖረዋል።አሊያ ግን ይህ ቦዶነት እንደ ጋሼ ፒፓ ነግ ተነገ ወዲያ የሃፍረት ሸማን ያከናንባል።የእነሱ ከሕዝቡ ችግር ጋር ዝምድና የሌለው ፅሁፍ እንደ ጋሼ ፒፓ መፅሔትና ጋዜጣ ማንም ሳያነበው የድኅረ ገፅ ማሞቂያ ሆኖ ይቀራል።

ስለኛ የሚስብ በሰላም ይክረም